

ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል እጅ መንሻ ይዘው እንደሰገዱለት ።

# ትንሣኤ

እንኳን
ለብርሃነ
ልደቱ
አደረስዎ!



የሰላም መልአክ ቅዱስ ገብርኤል

ቁጥር 15 ፲፱፻፸፩ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና ፤
ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና ፤
ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን
ተከፍሎ የነበረው ይሻራል ።

ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር ፤
እንደ ልጅም አስብ ነበር ፤
እንደ ልጅም እቈጥር ነበር ፤
ጕልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን
ጠባይ ሽሬአለሁ ።
ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ
እንደምናይ ነን ።
በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን ፤
ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ ፤
በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ
እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ ።

እንዲህም ከሆነ ፥ እምነት ተስፋ ፍቅር
እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ ፤
ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው ።


፩ ቆር ፥ ፲፫

ይህ ታሪክ የተቀዳው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው ይህን ካነበቡ
በኋላ አንድ አዲስ ኪዳን ገዝተው እንዲያነቡ እናሳስባለን ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ።
የፖስታ ሣጥን ቍጥር 30750
ስልክ 12 20 33
አዲስ አበባ ።
BBON Amh. LOVE
2nd Printing BSE - 1977 - 30M.



www.ethiopianorthodox.org



## ምእመናን ሆይ !

በክርስቶስ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ሀብቶቿ ምእመናን ናቸው የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን እያፈረሰ ጉዳት አስከትሏል ፤ የሥላሴ ክርስቲያን ፍቅር የጠራችሁ ፤ ለቤተ እግዚአብሔር መጠገኛ እጃችሁን እንድትዘረጉ ተጋብዛችኋል ።

የአድባሩ ኮሚቴ

